## የመጽሐፍ ፡ ክለሳ ፡ (ትችት) ።

ስቲቨን ፡ ሎወንሽቲን ፡ ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ስተዲ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፔናል ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ ዛሬ ፡ ሊደሰቱ ፡ ይገባቸዋል ። ባ፲፱፻፵፩ ፡ ተጀምሮ ፡ አሁንም ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሰናዳት ፡ (ኮዲፊኬሽን) ፡ ከጀመረ ፡ ወዲህ ፡ የአዳዲስ ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ጽሑፎች ፡ መታተም ፡ በመስፋፋት ፡ ላይ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ (የቀዳማዊ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ቅርንጫፍ ፡ በሆነው) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ኢንስቲትዩት ፡ በሚታተመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ አጫጭር ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ጥናቶች ፡ ወጥተዋል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የሚታተመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ጉዳዮችንና ፡ ሌሎችንም ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተሰጡ ፡ ውሳኔዎችን ፡ እያተመ ፡ ያወጣልናል ። ይልቁንም ፡ ውሳኔዎቹ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ታትመው ፡ ባለመውጣታቸው ፡ የተፈጠረው ፡ ጉድለት ፡ ለሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ በጣም ፡ ተሰምቷቸው ፡ ነበር ። ሕግ ፡ መኖሩ ፡ የሚታወቀው ፡ በየቀኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሲሠራበት ፡ እየታየ ፡ ስለሆነ ፡ የውሳኔዎቹ ፡ መታተም ፡ እንዲቀጥል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ይብሉጥ ፡ እንዲስፋፋም ፡ ምኞታችን ፡ ነው ። ይህ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ፕሮግራም ፡ የሚካሄደው ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ሲሆን ፡ ፋኩልቲውን ፡ በጣም ፡ የሚያስመሰግነው ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ውሳኔዎችና ፡ ጽሑፎች ፡ በየጊዜው ፡ ሳያቋርጥ ፡ መታተምና ፡ የማተሙም ፡ ሥራ ፡ እየተፋጠነ ፡ መሄድ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የደስታ ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ በተለይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ ከሁሉ ፡ በበለጠ ፡ የሚደሰቱበት ፡ ምክንያት ፡ አለ ። የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ባ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በማከታተል ፡ ሁለት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ መጽሐፎች ፡ አሳትሟል ። ለዚህ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክለሳ ፡ መነሻ ፡ የሆነውን ፡ የመጀመሪያውን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፉት ፡ በዚሁ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ አስተማሪ ፡ የነበሩት ፡ ስቲቨን ፡ ሎንሽቲን ፡ ናቸው ። ሁለተኛውን ፡ የጻፉት ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ የነበሩት ፡ ፊሊፕ ፡ ግራቨን ፡ ናቸው ። አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፔናል ፡ ሎው ፡ የተባለው ፡ የግራቨን ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ መጀመሪያዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ፹፩ ፡ ቁጥሮች ፡ የተጻፈ ፡ ዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፡ ነው ። የግራቨንን ፡ ማብራ

---

፩. ባ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከታወጀው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወዲህ ፡ (ባ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጸናው) ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ባ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጸናው) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ባ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጸናው) ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ (ባ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጸናው) ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ (ባ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጸናው) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ታውጀዋል ። የማስረጃው ፡ ሕግ ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ ይታወጃል ።

ሪያ ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተጻፉ ፡ ክለሳዎች ፡ ስላሉ ፡ ያሁኑ ፡ ጽሑፍ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክለሳ ፡ በሎወንሽቲን ፡ ጽሑፍ ፡ ብቻ ፡ ይወሰናል ። “ማቴሪያልስ” (“የተውጣጡ ፡ ጽሑፎች”) ፡ የሚሉት ፡ በአርእስቱ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላት፡ የሎውንሽቲንን ፡ መጽሐፍ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብ ፡ አሳምረው ፡ ያስረዳሉ ። መጽሐፉ ፡ (በመግቢያው ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ) ፡ የዩኒቨርሲቲውን ፡ ተማሪዎች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሐሳቦች ፡ ለማስተማር ፡ ይጠቅማሉ ፡ ብሎ ፡ ደራሲው ፡ ያጠራቀማቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ የያዘ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ጽሑፎች ፡ ከዚህም ፡ ከዚያም ፡ የተጠራቀሙ ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ (የውጭ ፡ አገር ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጨመሩበት ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ባለመገኘታቸው ፡ ነው ።) መጀመሪያ ፡ በፈረንሣይኛ ፡ ከተጻፈው ፡ (አቫን ፡ ፕሮዤ) ፡ እና ፡ ኦፊሲዩል ፡ ከሆነው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ከተጻፈው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ ምንባቦች ፡ እና ፡ በተጨማሪም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ግርን ፡ ግራቫን ፡ ካዘጋጁት ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የተወሰዱ ፡ ምንባቦች ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያው ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ እንደ ፡ መምሪያ ፡ ሳይጠቀምባቸው ፡ አልቀረም ፡ ተብለው ፡ የሚታመኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ ከሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ጽሑፎች ፡ የተወሰዱ ፡ አጫጭር ፡ መግለጫዎች ፡ (እነዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ የተወሰዱት ፡ ከአንግሎ ፡ ሳክሶን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ነው) ፡ በእርግጥ ፡ የተፈጸሙ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎች ፡ ምሳሌዎች ፡ እና ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲመልሷቸው ፡ የተጻፉ ፡ ጥያቄዎች ፡ ይገኙበታል ፡ ወዘተ ።

የጽሑፎቹ ፡ ብዛት ፡ የማይካድ ፡ ነው ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ፡ ወይ ፡ በተለይስ ፡ ተማሪው ፡ አይደነጋገርምን ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ያስደፍራል ። እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመመለስ ፡ መጽሐፉን ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ ያሻል ።

ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ውሳኔዎች ፡ በሰፊው ፡ ታትሞ ፡ መውጣት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ፤ ለዚሁም ፡ ሎውንሽቲንን ፡ ማመስገን ፡ ይገባናል ። ሆኖም ፡ ስለውሳኔዎቹ ፡ የወጣ ፡ ትችት ፡ የለም ። ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ነቀፌታ ፡ ለመሰንዘር ፡ ሳይሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ፤ ወይም ፡ ውሳኔዎቻቸውን ፡ ሁልጊዜ ፡ ያለምንም ፡ ቅሬታ ፡ መቀበል ፡ ይገባል ፡ ተብሎ ፡ ስለማያውቅ ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ማብራሪያ ፡ ምንኛ ፡ ጠቃሚ ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ሎወንሽቲን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ ማደግ ፡ የሚያሳዩ ፡ ጽሑፎች ፡ (ከመጀመሪያው ፡ ዕቅድ ፡ ረቂቅ ፡ በፈረንሣይኛ ፡ ከተዘጋጀው ፡ ረቂቅ/አቫን ፡ ፕሮዤ) ፡ ኦፊሴል ፡ ከሆነው ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ እትም ፡ እና ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ጽሑፎች ፡ የተወሰዱ ፡ አጫጭር ፡ ማስረጃዎች) ፡ ሰብስበው ፡ በመጽሐፋቸው ፡ በማሳተማቸው ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባል ።

ሆኖም ፡ የተቀሩት ፡ ጽሑፎች ፡ አመራረጥ ፡ ማደናገርን ፡ የሚያስከትል ፡ ነው።

ዋና ፡ ዓላማው ፡ ለጀማሪዎች ፡ መማሪያ ፡ እንዲሆን ፡ እታቀደ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከአውስትራሊያ ፡ ከካናዳ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ከጋና ፡ ከሕንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ከኬንያ ፡ ከኒው ፡ ዚላንድ ፡ ከናይጀርያ ፡ ከሱዳን ፡ ከታንዚንያ ፡ ከዩናይትድ ፡ እስቴትስና ፡ ከዛምቢያ ፡ የተገኙ ፡ ብዙ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ማስገባት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበርን? እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጥርጣሬ ፡ ቢገባው ፡ እውነት ፡ አለው ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ከተጠቀሱት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ሕጋቸው ፡ የኢትዮ

ጵያ ፡ የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ በተለይም ፡ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከተመሠረተባቸው ፡ የሕግ ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳቦች ፡ በመሠረቱ ፡ የተራራቀ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ በብዛት ፡ የተዘረዘሩት ፡ ዓይነታቸው ፡ የተለያየ ፡ ጽሑፎች ፡ ሊወዳደሩ ፡ መቻላቸው ፡ አከራካሪ ፡ ነው ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ እነዚህን ፡ ጽሑፎች ፡ ማወዳደር ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡ በእኔ ፡ አስተያየት ፡ ያለአንዳች ፡ መግለጫ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ጀማሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ከማቅረብ ፡ ይልቅ ፡ በተለይ ፡ በዚህ ፡ መስመር ፡ ለተራቀቁ ፡ ሰዎች ፡ ቢተውላቸው ፡ በተሻለ ፡ ነበር ።

ከሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ጽሑፎች ፡ የተወሰዱት ፡ ብዙ ፡ ጥቅሶችም ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥርጣሬ ፡ ይፈጥራሉ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ባያዘጋጁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አነስተኛ ፡ ጽሑፎች ፡ ራሳቸው ፡ ያረቀቁት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪካዊ ፡ አቋም ፡ ከጻፉት ፡ የሕጉ ፡ "አባት" ከሆኑት ፡ ከፕሮፌሰር ፡ ዣን ፡ ግራቭን ፡ ጽሑፎች ፡ የታወቀውን ፡ የስዊስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ካዘጋጁት ፡ ደራሲ ፡ ከሎገዝ ፡ ጽሑፎች ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ ከ"ፌሽ ፡ ገፑሪዲክ ፡ ስዊስ" ፡ ጥቅሶች ፡ መወሰዳቸው ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ለማብራራት ፡ ሲባል ፡ የአንግሎ ፡ ሳክሰን ፡ ሊቃውንት ፡ (እነ ፡ ሆል ፡ ሃርትና ፡ ሃርኖ ፡ የተባሉት ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ ቢገኙበትም) ፡ ስለ ፡ አገራቸው ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የጻፉትን ፡ መጨመር ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያደናጋግር ፡ ነው ። በተለይም ፡ መጽሐፉ ፡ የተዘጋጀው ፡ ያለምንም ፡ ጥርጥር ፡ በአንግሎ ፡ ሳክሰን ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ያልተመሠረተውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ለጀማሪዎች ፡ ለመግለጽ ፡ መሆኑን ፡ የተመለከተ ፡ የአንግሎ ፡ ሳክሰን ፡ ሊቃውንት ፡ ጽሑፍ ፡ መጨመር ፡ የበለጠ ፡ የሚያደናግር ፡ ሆኖ ፡ ያገኘዋል ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ ገና ፡ መጀመሩ ፡ ስለሆነና ፡ በተለይ ፡ ስለዚሁ ፡ ሕግ ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ግብራሪያዎች ፡ መረዳት ፡ ግድ ፡ ይሆንብናል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ይቀርብ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ትክክለኛነቱ ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ መረዳት ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ የሌለውን ፡ ጽሑፍ ፡ በታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ የተጻፈ ፡ ቢሆንም ፡ በቀጥታ ፡ መገልበጥና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማምጣት ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ዋና ፡ ዋና ፡ የሆኑትን ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳቦች ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ግልጽና ፡ እጥር ፡ ምጥን ፡ ባለ ፡ መልክ ፡ ለማስረዳት ፡ ሲባል ፡ ጠቃሚ ፡ ተብለው ፡ የተገመቱት ፡ ጽሑፎች ፡ በጥንቃቄ ፡ ከተመረጡ ፡ በኋላ ፡ መብራራት ፡ ያስፈልጋቸዋል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፤ ይህን ፡ አስቸጋሪና ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ የወደፊቱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመፍጠር ፡ ይረዳል ፡ ብሎ ፡ የሚገመተውን ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የተጻፈ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ በጥንቃቄ ፡ አስቀድሞ ፡ መምረጥ ፡ ያሻዋል ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ ፡ በየትኛው ፡ ሞዴል ፡ እንደሚጠቀም ፡ መወሰን ፡ ይኖርበታል ። የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ "ኮንቲኔንታል" ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራውን ፡ የኤውሮፓን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ እንደሚመስል ፡ አያጠራጥርም ። አንድ ፡ ኤሮፓዊ ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንዳፍታ ፡ ቢመለከት ፡ ባ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ከወጣው ፡ ከፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ከመ

ነጩት ፡ ብዙ ፡ ሕጐች ፡ አንዱ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያውኑ ፡ በቀላሉ ፡ ሊገነዘብ ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ይህን ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ። እውነት ፡ ነው ፡ ባ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) የወጣው ፡ የፈረንሣይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ብዙ ፡ ለውጥ ፡ ቢደረግበትም) ፡ አሁንም ፡ ይሠራበታል ፤ ግን ፡ አሁን ፡ ካሉት ፡ ከኤውሮፓ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጐች ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለውም ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ሁለቱን ፡ ሕጐች ፡ ማወዳደር ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውም ።

እንግዲያውስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ የሚመስሉት ፡ የትኞቹ ፡ ሕጐች ፡ ናቸው? የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ የተመለከታቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጐች ፡ ቍጥር ፡ ስፍር ፡ የላቸውም [2] ፤ ዋና ፡ መምሪያ ፡ የሆኑት ፡ ግን ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ፕሮፌሰር ፡ ጃን ፡ ግራቨን ፡ በጻፉት ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ (ሉውንሸቲን ፡ ገጽ ፡ ፰፻ ፡ ላይ ፡ ጠቅሰውታል) ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ይገኛል ፤ "የኮንቴንታልን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ በተለይም ፡ የዚህን ፡ አቋም ፡ ሞዴል ፡ ታላቁን ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሕጋውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ተወስኗል ፡ ዘመናውያን ፡ ከሆኑትና ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጣሉ ፡ ተብለው ፡ ከሚገመቱት ፡ ሕጐችና ፡ የሕግ ፡ ንድፎች ፡ ከነዚህም ፡ መካከል ፡ የስዋስ ፡ የጀርመንና ፡ የጣሊያን ፡ ሕጐች ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ሐሳቦችና ፡ መፍትሔዎች ፡ አግኝተናል ።" ይህ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያዘለ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ነው ። እነዚህ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሦስት ፡ ሕጐች ፡ (እነሱንም ፡ በጣም ፡ የሚቀርቡዋቸው ፡ ሌሎች) ፡ ምንም ፡ በጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ ቢለያዩም ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ የሕግ ፡ አዝማድ ፡ እንደሆኑና ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ በመሠረቱ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ ፕሮብሌሞችንና ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦችን ፡ በመመርመርና ፡ በመግለጽ ፡ አብረው ፡ የሠሩ ፡ መሆናቸው ፡ በሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ ሦስት ፡ አገሮች ፡ የሚገኘው ፡ ሕጋዊ ፡ ጽሑፍ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ስለሆነ ፡ ወሰን ፡ የለውም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፤ ስዊትዘርላንድ ፡ ውስጥ ፡ ከስቱስ ፡ እስከ ፡ ሃፍተር ፤ ጀርመን ፡ ውስጥ ፡ ከፎን ፡ ሊስት ፡ እስከ ፡ ቬልስል ፡ ኢጣልያ ፡ ውስጥ ፡ ከካራራ ፡ እስከ ፡ ቤትዮል ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተደረሱት ፡ ሞኖግራፎች ፡ (አነስተኛ ፡ ጽሑፎች) ፡ ማኑዋሎች ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ ታላቅ ፡ ድርሰቶቹ ፡ ተቆጥረው ፡ አያልቁም ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለመግለጽና ፡ ለማስረዳት ፡ በሚሞክርበት ፡ ጊዜ ፡ በመሠረቱ ፡ መጠቀም ፡ ያለበት ፡ በነዚህ ፡ ጽሑፎች ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ስል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሲጻፍ ፡ የእንግሎ ፡ ሳክሰንን ፡ ሕግ ፡ ከኮንቴንንታል ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በማነጻጸር ፡ አልነበረም ፡ አለማለቴን ፡ ማሳሰብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አይታየኝም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ይበልጣል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ መሰንዘሬ ፡ አይደለም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የማነጻጸር ፡ ሥራ ፡ ፍሬ ፡ ቢስና ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ። አስፈላጊው ፡ ነገር ፡ የትኞቹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጐች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በቅርብ ፡ እንደሚዛመዱ ፡ መወሰንና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ስለነዚህ ፡ ሕጐች ፡ በተጻፉት ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ በመጠቀም ፡ ተጨማሪ ፡ ሐተታ ፡ በማከል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ መግለጽና ፡ ማስረዳት ፡ ነው ።

እላይ ፡ የተባለው ፡ ሁሉ ፡ የሉውንሸቲንን ፡ ልፋት ፡ ለማንኳሰስ ፡ የታሰበ ፡ አይደለም ። እንዲያውም ፡ አዳጋችና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ስላልተነካ ፡ ነገር ፡ መጽ

---

፪. የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ሲወጣ ፡ ረቂቅ ፡ አውጪው ፡ የተጠቀመባቸውን ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዝርዝር ፡ በፔ ፡ ግራቨን ፡ አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፔናል ፡ ሎው ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ባለው ፡ መምሪያ ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፹፭ ፡ እስከ ፡ ፪፻፹፮ ፡ ይመለከቷል ።

ሐፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ መጀመሪያ ፡ በመሆናቸው ፡ ሎውንሽቴን ፡ መመስገን ፡ ይገባቸዋል ። ዓላማዬ ፡ ወደፊት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ መከተል ፡ ግዴታ ፡ የሚዘገበትን ፡ ዋናውን ፡ አቅጣጫ ፡ ማሳየት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ያቀረብሁት ፡ አስተያየት ፡ በጭራሽ ፡ በሐሳብ ፡ ላይ ፡ የሚዋልል ፡ (ቲኦሪቲካል) ፡ አይደለም ፡ እንዲያውም ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችል ፡ ነው ። የሎውንሽቴን ፡ ከላይ ፡ በተከተቀሱት ፡ የኮንቲኔንታል ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ (ማለት ፡ የጀርመን ፡ የጣልያንና ፡ እንዲሁም የስዊዘርላንድን) ፡ አለመጠቀም ፡ መሠረታዊ ፡ በለሆኑ ፡ አንድ ፡ አንድ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሳይናገሩ ፡ እንዲያልፉ ፡ አድርጎችዋል ። ደራሲው ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ስለ ፡ ተከለከሉት ፡ መንገድ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ተማሪዎችን ፡ በጥንቃቄ ፡ ከራሳቸው ፡ እንቅተው ፡ እንዲየስቡ ለማበረታታት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ የሚማረውን ፡ ተማሪ ፡ የሕግ ፡ ስውን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የአስተሳሰብ ፡ ዘዴዎች ፡ ለማስጨበጥ ፡ ማለት ፡ የአንድን ፡ ጉዳይ ፍሬ ነገር ፡ ከገለባው ፡ መርጦ ፡ ሕጉን ፡ ከፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እንዲችል ፡ ለማድረግ ፡ ተማሪው ፡ ጠንካራ ፡ ሠራተኛ ፡ እንዲሆንና ፡ ራሱን ፡ ችሎ እንዲሠራ ፡ ለማበረታታት ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ጥሩ ፡ አስተማሪ ፡ መሆኑ የሚታወቀው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዓላማ ፡ ሲኖረው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ዓላማዎች ፡ እግብ ፡ ለማድረስ ፡ ተማሪው ፡ በተለይም ፡ ጀማሪው ፡ ተማሪ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ በቅደም ተከተል ፡ የሚገኙበት ፡ መመሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ አያስፈልግም ፡ ወይ? በሎውንሽቴን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ የተወሰዱ ጥቅሶችና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ቢገኙበትም ፡ ቅሉ ፡ መጽሐፉ ፡ ያልተሟላ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እርግጥ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ አጠናቆ ፡ ለሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ጠቃሚ ፡ ምርምር ፡ እንዲያደርግ ፡ ይረዳው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ተማሪ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ መጽሐፉ ፡ የሳተውን ፡ ለማሟላትና ፡ ለጀማሪ ፡ ተማሪ፡ ግር ፡ የሚሉትን ፡ ነገሮች ፡ እንዴት ፡ ሊያስወግዳቸው ፡ ይችላል ።

የሚከተሉት ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ያለእንዳች ፡ መግለጫ ፡ የተዘለሉትን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ ለማመልከት ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ፡

(፩) ባ፲፱፻፶፯ ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ ይገኛሉ ። ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ወንጀለኛ ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ ያላቸውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ማስረዳት ፡ አያሻም ። በሎውንሽቴን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ስለነዚህ ፡ ሐሳቦችም ፡ ሆነ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ውስጥ ፡ መኖራቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ እንዳችም ፡ ነገር ፡ አልተጻፈም ።

(፪) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ "ሕግነቱ ፡ መሠረት" ይናገራል ። ይህ ፡ በኮንቲኔንታል ፡ ሕግ ፡ (የፈረንሣይ ፡ ሕግ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ) ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ መሠረታዊ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሐሳብ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ሎውንሽቴን ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ሐሳብ ፡ አንድም ፡ የጻፉት ፡ ነገር ፡ የለም ።

(፫) ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ እጅግ ፡ አሳሳቢ ፡ ስለሆነው ፡ ስለ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ዘዴ ፡ ይናገራል ። ሆኖም ፡ ሎው

ንሽቲን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከኮመን ፡ ሎውና ፡ ከኮንቲንታል ፡ ጽሑፎች ፡ በጣም ፡ አጫጭር ፡ ጥቅሶች ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ አልፈውታል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ከሚቀጣቸው ፡ አድራጐቶች ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላሉ ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ቅጣት ፡ እንዳይፈጸም ፡ በግልጽ ፡ ይከለክላል ። በሎውንሽቲን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ የአንዲት ፡ መስመር ፡ መግለጫ ፡ እንኳን ፡ አልተጠሰም ።

(፬) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፭ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ስለታወቁ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጸሙ ፡ አድራጐቶችን ፡ አይቀጣም ፡ ስለሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ እና ፡ ይህ ፡ ስለሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ይናገራል ። ተማሪው ፡ በከንቱ ፡ ይደክም ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሎውንሽቴን ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህ ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ አያገኝም ።

(፭) ቍጥር ፡ ፳፭(፪) ፡ "ሕግ ፡ መጣሱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የማይፈጸም ፡ ሲሆን ፡" ቍጥር ፡ ፴፫ ፡ "የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሊሠሩት ፡ የሚቻል ፡ ወንጀል ፡" ቍጥር ፡ ፴፩ ፡ ደግሞ ፡ "የኅብረት ፡ ወንጀል" ፡ ስለሚባሉት ፡ ወንጀሎች ፡ ይናገራሉ ፤ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ስለነዚህ ፡ ቃላት ፡ አንድም ፡ መግለጫ ፡ አይገኝም ። ወንጀሎች ፡ አጠር ፡ ባለ ፡ አቀራረብ ፡ እንኳ ፡ በየዓይነታቸው ፡ ለጊዜው ፡ ተከፋፍለው ፡ አልቀረቡም ። እንግዲህ ፡ አከፋፈላቸውንና ፡ ልዩነታቸውን ፡ ተማሪው ፡ ራሱ ፡ ይደርስባቸዋል ፡ ብለን ፡ በተስፋ ፡ እንተወውን?

(፮) በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ በዋና ፡ ወንጀል ፡ አድራጊውና ፡ በግብረ ፡ አበሮቹ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ በሚያነሳሳው ፡ ሰውና ፡ በአባሪ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እጅግ ፡ ባጠረ ፡ አኳኋን ፡ ተገልጧል ፡ (ቍጥር ፡ ፴፪ና ፡ ተከታዮቹ) ።

(፯) ከብዙዎቹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ (ለምሳሌ ፡ ቍ ፡ ፵፭(፪) ፡ ፷(፭) ፡ ፷(፪) ፡ ፸፭ ፡ እና ፡ ፸፩) ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ በወንጀሎቹ ፡ መፈጸም ፡ ስለ ፡ ተጐዳው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ በግልጽ ፡ ይናገራል ። በተለይም ፡ በኮንቲኔንታል ፡ ሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የተተቸበትን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትልቅነት ፡ ማስገንዘብ ፡ አያስፈልግም ። ሎውንሺቴን ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለጀማሪዎች ፡ ማብራሪያ ፡ የሚሆን ፡ የጻፉት ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ የለም ። በተለይም ፡ አፊሲዬል ፡ በሆነው ፡ በእንግሊዝኛው ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ ቍጥሮቹ ፡ አጠራጣሪ ፡ ትርጉም ፡ ስላላቸው ፡ ማብራሪያ ፡ መስጠት ፡ ያሻ ፡ ነበር ።

(፰) የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ከ፷፯ ፡ እስከ ፡ ፸፫ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ቍጥሮች) ፡ "የማያስቀጡና ፡ ይቅርታ ፡ የሚያሰጡ ፡ ሁኔታዎች" ፡ የሚል ፡ አርእስት ፡ አለው ። የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚያሻው ፡ ክፍል ፡ እንደሆነ ፡ ያውቃሉ ፤ አንድን ፡ ተከሳሽ ፡ ከቅጣት ፡ ሊያድኑ ፡ የሚችሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ከዚህ ፡ ክፍል ፡ ይገኛሉ ። ግን ፡ "የማያስቀጡት" ፡ የትኞቹ ፡ "ይቅርታ" የሚያሰጡት ፡ ደግሞ ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ ለተማሪው ፡ የሚገልጽለት ፡ ማነው? ሕጉን ፡ ያዘጋጀው ፡ ሊቅ ፡ በአርእስቱ ፡ ውስጥ ፡ በሁለቱ ፡ ቃላት ፡ ለምን ፡ እንደ ተጠቀመ ፡ የሚገልጽለት ፡ ወይም ፡ ሊገልጽለት ፡ የሚሞክረው ፡ ማነው?

(፱) የቍጥር ፡ ፵ ፡ ሁለተኛው ፡ አዲስ ፡ መስመር ፡ ከቅጣት ፡ ለማዳን ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑት ፡ የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ (ምክንያቶች) ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ ቢሆኑ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አይተላለፉም ፡ ይላል ። ይህ ፡ እንግዲህ ፡ የግል ፡ በሆኑትና ፡ የግል ፡ ባልሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነትና ፡ ልዩነቱም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ እንደሚያስከትል ፡ ለተማሪው ፡

መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ፡ ማለት ፡ ነው ። እርግጥ ፡ አዳጋች ፡ ሥራ፡ነው ፡ ግን ፡ መደ ረግ ፡ አለበት ። መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ካንዲት ፡ ገጽ ፡ መግለጫ ፡ በስተቀር ፡ ስለሁለቱ ፡ ልዩነት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይገኝም ።

(፲) የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የወንጀል ፡ አፈጻጸም ፡ አካ ባቢ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ ክፍል ፡ ለያይቶ ፡ ቅጣትን ፡ የሚያከብዱ ፡ ወይም ፡ የሚያቃልሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ያልሆኑ ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ ከፋፍሏቸዋል ። አከፋፈሉ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚያሻውና ፡ አዳጋች ፡ እንደሆነ ፡ ለመገንዘብ ፡ ረጃጅሞቹን ፡ ከቍጥር ፡ ፴፱ ፡ እስከ ፡ ፹፬ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ (ከዚያም ፡ የተጠቀሱትን ፡ ቍጥሮች) ፡ ማንበብ ፡ ይበቃል ። አሁንም ፡ ሎውንሽቲን ፡ ተማሪው ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ እርዳታ ፡ በራሱ ፡ ጥረት ፡ በቍ ፡ ፴፱—፹፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ ሳያብራሩ ፡ አልፈውታል ።

ብዙ ፡ ሌሎች ፡ ምሳሌዎችን ፡ መስጠት ፡ ይቻል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አጭር ፡ ጽሑፍ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መደምደም ፡ እና ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ማጠቃለል ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የተዘለለውን ፡ ነገርና ፡ ጉድለቶችን ፡ ለማውጣት ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ ሎውንሽቲን ፡ እንዳደረጉ ፡ ስለአንድ ፡ ያልተነካ ፡ ነገር ፡ የተጻፈ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጉድለቶች ፡ ስለማይታጡበት ፡ ነው ። የጽሑፉ ፡ ዓላማ ፡ (ምንም ፡ እንኳ ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ የሚገኘውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በሙሉ ፡ ለመግለጽ ፡ በቂ ፡ ባይሆኑም) ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የተውጣጡ ፡ ጽሑፎች ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ ተጠራቅመው ፡ እንዲቀርቡ ፡ በደስታ ፡ ለማብሰር ፡ ነው ። ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ በግምት ፡ ስምንት ፡ ዓመታት ፡ አልፎታል ፡ ስለዚህ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ሕጉን ፡ ማብራራትና ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ (አቋሙን) ፡ መግለጽ ፡ መጀመር ፡ ያለባቸው ፡ ይመስለናል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ የተከተለውን ፡ መስመር ፡ በጠቅላላው ፡ አቀራረቡንና ፡ አንዳንዶቹንም ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ማጥናት ፡ አለባቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ለቀረቡላቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ለሚሰጣቸው ፡ የተውጣጡ ፡ ጽሑፎች ፡ ሎውንሽቲንን ፡ ማመስገን ፡ ይገባቸዋል ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ የሎውንሽቲንን ፡ መጽሐፍ ፡ ምርኩዝ ፡ በማድረግ ፡ በመሻሻል ፡ የተዘጋጀ ፡ ጽሑፍ ፡ የምናይበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።